ረጅም ልቦለድ

፩ ረጅም ልቦለድ በገዘረው የሚቀረብ ሥራ ነው ዝርው ስንል (ክለሳ)

1. መደበኛ አምድ አለው፣ እንደ ግጥም በአሸቆልቋይ አምድ እየተሸነሸነ እይቀርብም
2. አስተማማኝና ዘላቂ ሥልተ ዜማ የለውም
   - አልፎ አልፎ ቡከሰትበትም ከግጥም ባሕርይ የሚወሳው ነው
   - ይህም ቢሆን ለአስረጅነት የሚበቃ አይደለም።
3. ተጠያቂነትን ጠብቀው በሚፈሱ የሐሳብ ዘለላዎች ይደራጃል።
   - ሰዋስዋዊ ሥርዓታቸው የጠበቀ ዐ.ነገሮች
   - እርስ በራሳቸው የተያያዙ መሆናቸው በግልጽ የሚታዩ ርእስ ጉዳዮች
   - በቂ ማብራሪያዎች ይሰገሰጉበታል
4. የደራሲው አሻራ ጐልቶ ይታይበታል
   - ቃላት ምርጫው ሥነ ሐረጋዊ መዋቅሮቹ፣ ሐሳብ አደረጃጀቱ የደራሲውን (የጸሐው የአጻጻፍ ሥልት ይጠቁማል)
5. ሐሳብ በነፃ ለማደራጀት ሰፊ ዕድል ይሰጣል።

የተለያዩ የአሐሳብ አቀነባበር ሥልት ይጠቁማል

ወጥ የሆነ ሥልት ውስጥ መግባትን አያሰገድድም

ሐሳብ አደረጃጀቱ ፈተጥሮአዊ መንገድን የተከለ ነው፣

፪ የትረካ ማቅረቢያ ዘይዎች (ክለሳ)

ገለፃ፡- ቁጣዮችን አስረጅዎች ተመልከቱ

አጅ
1. እፍታ 1991፣ 117-118
2. ደም በደም 1993፣ 43-45
3. አደፍርስ 1962፣ 26
4. አደፍርስ 1962፣ 30 አደፍርስ 67
5. ገዐረ 1998፣ 38
6. ግራጫ ቃ 1997፣ 191
7. አርአአ፣ 1939፣ 93፣ 112፣ 122፣ 134፣ 138
8. ደርቶጋዳ 2001፣ 32-33

❖ በገለፃው ውስጠ ሊመረመሩ የሚገባቸው ጉዳዮች

1. እየገለፀ ያለው ማነው?

- ደራሲው (እፍታ 117-8፤ አደፍርስ ፣ 26)
- ገጸባሕሪያት (አደፍርስ 1962፣ 67 ግራጫ 191

- ደራሲው ሲገልጽ ራሱን ይሰውርና መንፈስ ይመስላል፣ ሲመን፣ የነበረበትን ብትና የተገኘበትን ምክንያት አይነግረንም የተመለከተውን <u>የስሜት አዝማሚያ፣ የነገሮች አኳኋን፣ አካላዊ ጉዳዩች፣ ከስተቶችን</u> ይገልጣል፣ የስተዋውቃል።

2. እየተገለፀ ያለው ነገር ምንድ ነው?
   - የስሜት አዝማሚያ (አርአያ 134፤ ግራጫ 37፤ ትኩሳት 80፤ ጉንጉን 82)
   - ሰብአዊ አቋም (ስብእና፣ ግብረገብ፣...) (አርአያ 138፣)
   - አካላዊ ጉዳዩች (አርአያ 93፣ ትኩሳት 2000፣ 6፣18)
   - ድርጊያዎች/ሁነቶች (ንቅናቄ፣ ትወና...) (አለቀ በቃ፣3 ከሰማይ የወረደ ፍር 202፣ 93)
   - የዕውነታ/የተሞክሮ ደራዎች (ገዐራ 252-53፣ ቆንጆዎቹ 1989፣60)
3. ፋይዳው ምንድነው?

   - የምናብ ዕይታውን ማገዝ ጉንጉን 1982፣ 84
   - የተደራሱውን አረዳድ ቀላል፣ የተቀላጠፈና የተለጸ
     - የሴራው አደራር
     - የገጸባሕሪያቱ
     - የትረካው ፍሰት
   - አዝማሚያዎችን ለመቀየሰ ያግዘዋል።

<u>ጥንታዊ አዝማሚያ</u>/ተረታማ አቀራረብ

ደራሲው ጭብጥ አነፍናፊ ስለሚሆን ለጭብጡ ስርይት ሲባል፣ የገጸባሕሪያትን ማንነት በተመለከተ ተደራሲያን የለየለት አቋም እንዲኖራዋቸ አብዝቶ ይጥራል።

<u>ዕኩይት</u> በተደራሲያን እንዲነቀፉ፣ እንዲጠሉ፣.... ያጥላላል፣ ያብጠለጥላል፣ አቃቂር ያወጣላቸዋል።

❖ የተሸጐደጐደ አሰልችነት የሚታይበት፣ የተገለፀ አቋም የለው

አጅ 1. ጦቢያ 1900፣ 37-8
2. አርአያ 1939፣ 140-42፣
3.

ሰናይት በተደራሲያን ዘንድ እንዲወደዱ፣ ሲቻልም በአርአያነት፣ በምሳሌነት፣ እንዲጠቀሱ፣ ሰለባነታቸውም በአስረጅነት እንዲጠቀስላቸው ገለፃው ያወድሳል፣ ገፀባሕሪያቸውንም ያጸድቃል።

- ዘመናዊ አዝማሚያ/ገለጻ ማሳየት

❖ ደራሲው ዋና ሕልሙ ሕይወትንና ገመናዋን ገልጦ ማሳየት ነው

- በመጥፎ የሚየጣጥላቸው ወይም በበጎ የሚዘክራቸው አካላት አይኖሩትም
- ገለፃው ዕውነታውን በመዘንጠል ፍርዱን ለሌሎች መተው ነው።
- ገለፃው ከፈራጅነት ይልቅ አፈራራጅነቱ ይጐላል።

አጅ፡- ደርቶጋዳ 2001፣ 32-33

ግራጫ 396

አጅ 1. ከሰማይ የወረደ ፍርፍር 2002፣፣93፤ 162-7

2. አደፍርስ 36-37

3. ማኅሌት 1981፣ 63፣ 103፤ ማኅሌት፣ "ኤልዛቤል"

4. ሰርፍራፊ ከአንዶች "ስህተት"

❖ ሆኖም አንዳንዴ ደራሲው/ተራኪው የሚጠላውን ገጸባሕሪያት እንድነጠላው ለማድረግ ያልምና ስውር ተጽዕኖ ሊፈጥርብን ይችላል።

አጅ 1. ጉንጉን 91፤

ምልልስ፡- በገጸባሕሪያት መካከል ያለ ሥነልሳናዊና ተያያዝ ግብአቶች

- ሥነልሳኑ ተራክበውን የማክልና ተየያዥ ግብአቶቹ ያበለጽጉታል

❖ ተራክቦው ሦስት ጉዳዮችን ይይዛል

እነሱም

መአ	መል	መተ

❖ ተክባው መልዕክት ማፍለቅን ብቻ ሳይሆን ግበረ መልስን ግድ ይላል፤ ከሦስቱ አንዱ ከተጓደለ ምልልስ ይቆማል

❖ መልዕክተ አፍላቂው በሐተታ፣ በጥያቄ በአጋኖ መልዕክቱን ያሻግራል

በቁጣ

በልመና ወዘተ

❖ መልዕክት ተቀባዩ በዝምታ፣ በእንቅልፍ፣ በሃቢብ፣ በገቢር (ድርጊት በማከናወን፣ አካልን በማንቀሳቀስ፣ ገጽታን በመጠቀም) ግበረ መልስ (አዎንታ፣ አጸፋ፣....)ይሰጣል።

❖ በሁለቱ መካከል የተራ ፍጆታ ልውውጥ ይኖራል

- ተራ ፍጆታ የተመላላሾቹን ሕሊናዊ (የዕውቀት ደረጃ)፣ ወዘተ ደራጃዎች ቁምር ያሳያል።
- ሰፊ/ጠባብ የንግግር ዕድል ወይም አቻነት በልቦለዱ ታሪክ ውስ ልዩ ስማት ሊፈጥር ይችላል።

- የገጸባሕሪያት ቋንቋ በብ እናታቸውንና ማንነታቸውን ገልፆ ያሳያል

አጅ 1. አደፍርስ 1962፣ 6-፤ 39-43፤ 60-69

2. እፍታ 1991፤ 87-110

3. ገዐረ 57-8፣

4. ግራጫ 1997፣ 232-5፤

<u>ንግር</u>፦

❖ ብዙውን ጊዜ በልቦለዱ መነሻ አካባቢ ይቀርባል፣ የጉዳዮችን አዝማሚያሃ የገጸባሕሪያትን ጣፈንታ ከወዲሁ ጠቁሙ ተደራሱውን ለማጓጓት ሲባል።

<u>አጅ</u> ደም በደም 1993፣ 3

❖ ልቦለዱ የወሰኑ ገጾች ከተራመደ በኋላም ሊቀርብ ይችላል።

<u>አጅ</u> ገዐረ፣ 43 (..... የተገፋ እንጀራ ይስጥህ .....ጥላህ እንደትልቅ ሰው ከባድ ነው።)

❖ የት መጣው?

- ትውፊታዊ መሰረት አለው
- ሥር ሰደድና ወጫቂ ቡድናዊ (collection) ነው።
- ሰዎች ነገር፣ የወደፊት ጠፈንቃን የማወቅ ጭንቀታቸው አሁን በሚገጥሟቸውና በሚመለቷቸው ጉዳዩች ውስ የተመሠጠረ አማልዕክታዊ/መንፈሳዊ ማመላከቻ አለ ብለው እንዲያምኑ አስገድዷቸዋል።

- ገጠመኞቹ ተምሳሌታዊ ፋይዳ እንዳላቸው አድርገው ያምናሉ

ዕድልን ማመልከቻ ናቸው ተብለው ይታመ

መየኢውን ዓለም ይታመናሉ።

❖ አቀራረቡ/ብልሃቱ

- ለመመልከትም ሆነ ለመተርጐም ልዩ ብቃትና መንፈሳዊ ተቀብኣ ያላቸውን ሰዎች ያሻል፤ ለተርታ ሰዎች ተምሳሌቶቹ ተርታ ሊሆኑ ይችላሉ።
- በአዋጅ፣ በፋይና በተገለጠ መንገድ ላይሆን በምሥጢር ይቀርባል
- አመለጥሮው ተምሳሌትን፣ መለኮታዊ ግምቶችን፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን፣ ሁኔቶችን (ማስነጠስ፣ ስርቅታ....) በመጠቀም ይቀናበራል።
- ስለሆነም በልቦለድ ውስጥ <u>ንግርን</u> ልብ የሚሉት በትውፊቱ ዙሪያ ግንዛቤ ያላቸውንና በጥበቡ አረዳድ ልበና ልቡና የተሰጣቸው ናቸው።

❖ በልቦለዱ ውስጥ ጥበባዊ ፋይዳው.....?

- የዐበይት ገጸባሕሪያቱን መዛለቂያና የማታ ጣፈንታ በተመለከተ አቅጣጫ ይሰጣል
- ልብና ልቡና ለተቸረው አንባቢ የንባብ ጉጉትን ያጭራል፤ የፍጻሜው የመድረስ አመሮቱን ይቀሰቅሳል
- ከልብ ሰቀላ ብልሃቶች አንዱ ይሆናል።

❖ ሆኖም በሁሉመ ልቦለዶች ውስጥ የግድ ይምጣ አይባልም

<u>ምልሰት</u>

❖ በትረካ ሂደት "የዚህ መነሻው ምንድነው" በሚል ዓይነት ጥያቄ የደራሲውን ሕሊና እየተከተተለ የሚፈትር ጥብቅ/ብርቱ ጉዳይ ይኖራል።

- ተደራሲውን ፋታ ይናሳዋል፤ ይከታተለዋል። መልሱን እስከሚያገኝ እረፍት ያጣል
- አንድ የንባብ አምሮት መቀስቀሻ፣ የጉጉት ማጫሪያ ነው። (ልክ አንድ ሰው "የምነግርህ አንድ ጥብቅ ምሥጢር አለኝ" እንዳለ ብጤ ስሜታችን ለማወቁ ያቆበቁባል)
- ምሥጢሩ ተጐርዶ የቀረ የአንድ ቁም ነገር አካል ነው።

❖ ይህ ጥያቄ የሚጫረው ደራሲው ይሁነኝ ብሎ ጐርዶ ከሚያስቀረው የገጸባሕሪያት ጠቃሚና ፊርጣማ ተሞክሮ ነው።

- ተሞክሮው የሚጐረደው ፋይዳው አንሶ ላይሆን እንዲያውም ከቁልፍኑቱ፣ ከአንገብጋቢነቱና ከወሳኝነቱ የተነሳ ተደራሲው በጉጉት እየጠበቀ እስኪሰማው እንዲቋምጥ ነው።
- ያ ተሞክሮ በገጸባሕሪያቱ የአሁን ሕይወት ውስጥ ቁልፍነት ይኑረው እንጂ በይዘታው (በዙሪያው መለስ ድርሻው) ግን ልቦለዱ ከሚያተኩርበት መጠን ርዕይ የጠበበ ክልል (ሽፋን) ያለው ነው።

አጅ 1. <u>በደም በደም</u> መጽሐፍ የልቦለዱ ማተኮሪያ ዓለም <u>የአየለ የበቀል</u> ጥማት ነው፣ <u>የአባትን ደም የመመለስን ዓለማ</u> ለማሳካት አበግቡ የተካሄደበት ዓለም ነው።

- ታሪኩ በዚያ ግብግብ ውስጥ ሲያልፍ ወደኋላ ተመልሶ የሚያስቃኝን ያለፈው ተሞክሮ ከባድ ጥላና ሥነልቡናዊ ጠባሳ አለ።

<u>ቅድመ አየለ</u> <u>የአየለ ዓለም (ዘመነ አየለ) ግብግብ</u>

- ተቀንጭቦ የቀረበ - በዝርዝርና በጥልቀት የሚተረክበት
- ዋናው ገጸባሕሪይ የሌለበት - ዋናው ገጸባሕርይና ትረካው ሚናው ጐልቶ የወጣበት
- የቦካው ቁርሾ መንስኤ - የትግልና የድሉ ስንክሳር የሚነበብበት
- ፍንጭ ሰጥቶ የሚሰወር

❖ አንዳንድ ዘመናዊ ልቦለዶች አጠቃላይ ታሪካቸውን በመቀለባበስ ያራምዳሉ።

- ታሪኩን ከመነሻው ሳይሆን ከመሐል ቦድሰው ወይም ከመድረሻው ቀልብሰው ይጀምራሉ።

- ከዚያም ውሉ እንዳይጠፋብን እየተጠነቀቁ ወደፊት ወደኋላ በማቀለባበስ ይተርካሉ ታሪኩ ሲጠቃለል ትክክለኛ ፍሰቱ በውስጣችን ሥርዓት ያገኛል
- በእንዲህ ዓይነት ልቦለዶች ተደራሲው ጉጉ፣ አስተዋይና ብጥለጣሽ የሚመስሉትን ታሪኮች የማገናዘብ፣ የማወሪረስና የማቀናጀት ብቃት ያለው መሆን ይጠበቅበታል።

<u>አስረጅ</u>

የይስማዕከ ወርቁ ሥራዎች የዚህ ባሕሪይ አላቸው።

1. ዲርቶጋዳ ታሪኮቹ በቦታም፣ በጊዜም፣ በሁኔታም የተበጣጠሱ የሚመስሉ

❖ ወደ ኋላ ሄዶ የ 60 ዎቹ የገጠመኝ የተሞክሮ ዝንቆችን ይዟል የተሞክሮ ቁራ በማንሳት ጥቂት ገጾች ይራመዳል ("አመክንዮ" በሚል ርእስ)

- ተመልሶ በገጽ 19 ላይ ወደ ቅርቡ ዘመን ይመጣና የልቦለዱን የታሪክ እምብርት ይነካል (ፔ በማለት)

❖ እንደገና ወደ ቴሌቪቭ ያነጉደናል፣ ወደ ሲጻራና አናንያ

- በዚህ ሥር የሚራዥና የሲጻራ የልጅነት ዘመን ይቀርባል

ታሪኩ በዚህ መልክ ኋላና ፊት እየተገለመጠ ይተረካል።

የአሥራት ከበደ የምሽት እንግዳ

የምሽት እንግዳ

❖ ታሪኩ በማክዳ ናሁሰናይና በነቢዮ ሚልኪያስ ትውውቅ ይነሳል።

- ከዚያ በኋላ የእሱን ይቀለሳል፤ ክምኒልክ ጀምሮ ያለውን የብርሃኔ ልዑመ ልሳንን ታሪክ መካተት ይጀምራል
- አያይዞ የብርሃኔ የፈረንሳይ ሀገር ሞትና የእሱን ንብረት ውርስ እንቆቅልሽ ያነሳል (የኃይለ ሥላሴ ዘመን)
- እንቆቅልሽ በአቶ ሰይፉ የአቋራጭ ክብረት ምኞት የሚወጠን ነው
- እንቆቅልሹም በ"ውክልና" ሰበብ የሚሴር ነው።
- እንደገና ወደ ነቢዮ ዘመን ይመለስና የሰይፍና የነቢዮ ግብግብ ይጀምራል ነቢዮ ጥቃት ይሰነዝርበትና ሆስፒታል
- ከረጅም ታሪክ በኋላ ተመልሶ (ገጽ 222) ወደ አቶ ሰይፉ የቀድሞ የውርስ ሽፍጥ ይሄዳል፤ ፍንዳታ ወቅር

❖ የብርሃኔ ወንድሞች አለቁላቸው

- ገጽ 226 ላይ ወደ ነቢዮ ዘመን ይመልሰናል

❖ ሁለቱ ታሪኮች በኤፊሶን ከተማ በአንድ የዘመንና የቦታ መቼት ሲጋጠሙ ታሪኩ ያበቃል።

ማሳሰቢያ

1. ምልሰት፣ በዛሬው ማንነት ላይ ግልጽ ተፅዕኖ ያላቸው የቀድሞ ተሞክሮዎች በትውስታ መልክ ተቀናብረው የሚነገሩበት ነው።

2. ተሞክሮዎቹ

አዳማዊ ባሕርይ ሊኖራቸው ይችላል፤ ከተድላ ወደ ፍዳ

❖ የቀድሞውን ፈንጠዝያና ፍስሐ በማስታወስ ከዚያን መሰል ሕይወት ወደ ድቀት የመሩትን ተሞክሮዎች ያሳያል

❖ የስሜት ስብራት፣ የሥነልቡና ቀውስ፣ የህብት ድቀትና የክብር መዋረድ፣ ወዘተ የተፈጠሩበትን ሁኔታ እየገመገመ ይሄዳል

❖ ሰብአዊ ዝቅተት፣ ብካይና ራሮት ያደረሱትን ስብራት ያሳያል።

አጅ

ጠቢያዊ ባሕርይ የለውም አለ፤ ከፍዳ ወደ ተድላ (ፍስሐ)

❖ አስቀድሞ መጠነ ሰፊ የሆነ መከራና ሰቀቀን ይኖራል።

❖ በሂደት ግን ዓለም እየተረጋጋ ሄዶ በሁለንተናው ዕርቅ ይወርዳል፣ ሰላም፣ ይሰፍናል፡

አጅ የምሽት እንግዳ

ኢዮባዊ ገጽተ ያላቸውም አሉ።

❖ ምልሰቱ የቀድሞው ዘመን በጐ እንደሆነ ያሳያል።

❖ በመሐል ግን ግብግብ የጠነከረበት ዓለም፤ በቀውስ የተሞላ ሕይወት ዓለመ ይወጣታል።

❖ ሆኖም በገጸባሕሪያቱ ትዕግሥትና ተጋድሎ ዓለሙ መለሶ ይረጋጋል።

አጅ

3. የምልሰት ተሞክሮዎች ባጭሩ የሚቀናበሩ ሆነው፣ በትረካው ውስጠ ግን ቁልፍ ሥፍራ ይኖራቸዋል። የታሪኩ የደም ሥር ናቸው ቢባል ያስኬዳል።

❖ የጥላቻተን፣ የፍቅራችን፣ የትዝብታችን፣ የአደናቆታችን መሰረት ገዝፎ ይመጣበታል።

4. በአቀራረቡ በሳጋ መልክ (አጅ የምሽት እንግዳ) ወይመ በመደዴ አቀራረብ ሊተረክ ይችላል።

(የገጸባሕርያት አሰያየም ማዕቀፎች አመላመል)

የገጸባሕርያት አሰያየም/አሳሳል ማዕቀፎች

❖ ገጸባሕርያት የልቦለዱ ዓለም ባለጉዳይ አካላት ናቸው።

❖ የልቦለድ ደራሲ ለሥራው የተዋጣ ሚና ይጫወቱልኛል የሚላቸውን ገጸባሕሪያት ከሰው ዓለም ወይም ከሌሎች ዓለማት ሊመለምል ይችላል

❖ በሚከተሉት ሥራዎች መካከል ያሉትን ገጸባሕርያት እንመልከት

አጅ 1 የሱልጣኑ መጐናጸፊያ /የአገልጋዮ ማታለየ/ ለጋሱ ተማሪ

አጅ 2 አንዲት ዓይጥና አንድ ገበሬ (ጽጌረዳና ደመና)

አጅ 3 በማር ጠብታ ሀገር ተመታ (የውሻና ድመት ተመሳሌታዊነት) በውሾች ጠብ የተቀሰቀሰው ደም መፋሰስ

❖ ከአሳሪጅዎች እንደምናስተውለው፣ ገጸባሕርያት ከተለያዩ ምንጮች ሊቀዱ ይችላሉ። እነሱም ከአምሳያዎቻችን መካከል፣ ከሌሎች ፍጥረታት መካከል።

1. ምሳያዎቻችንን መመልመል፡- ላባለጉደዮቹ ቀጠተኛዎቹ እኛ ናቸው። ጉዳያችንን እኛኑ በሚመስሉ አካላት ላይ ተሰሎ እናገኝዋለን። እኛን አመሳስላቸውም።

ሀ. በሕገ ባሕሪያቸው ሰው ሆነው የተፈጠሩ፣ በአካል በግብር ቁርጥ ሰው የሆኑ የሰው አካል የተላበሱ፣ የሰው ርኀራሄ፣ ጭካኔ፣ ሕገልቡናና ባሕሪያት ያሏቸው።

ለ. በተሞክሮአቸው

- ቢጋቡ፣ ቢዋለዱ፣ ቢያምኑ ቢክዱ፣ ቢጸኑ-ቢወወድቁ፣ አድርገው ነው። ጉዳያቸው የእኛው ዓይነት ጉዳይ ነው።
- በዕጣ-ፈንታቸው፣ ጽዋ-ተርታቸው ቢንጋደድ ቢቃና፣ ቢጸድቁ ቢከነኩ፣ ድል ቢያደርጉ ሰለባ ቢሆኑ ያው ለእኛው የጣፈው ዕድል ድርሻ ያጋጥማቸዋል። በራሳችን በጐረቤታችን፣ ለወገናችን የምናስተውለው ነው።

❖ ገጸባሕሪያቱ ከምናባዊነታቸው ይቅል ጉርበትናቸው፣ ጓደኛነታቸው፣ ዝምድናቸው ወይም እኛን መሆናቸው ገኖ ይሰማናል።

❖ በርካታ ልቦለዶች የሚቀርቡት ከዚህ ዓለም በሚመለመሉ ገጸባሕርያት ነው።

❖ በዚህ መልክ የሚመለመሉ ገጸባሕርያት ከተምሳሌትነታቸው ይልቅ አስረጅነታቸው ይገሎላል።

- ልክ በነባራዊ ዓለም የአንድ ሰው ጥብቅ በጐ/ክፉ ተሞክሮ ለእኛ እንደ ገጠመኝ አስረጅ እንደመጠቀሰው ሁሉ ማለት ነው።

  ልክ እንደ ጀጋማ ኬሎ የበጋው መብረቅ 2004 ዓይነት ማለት ነው።

  ልክ እንደ የነጋሶ መንገድ (ዳንዲ)፣ 2003 ዓይነት ማለት ነው።

  ልክ እንደ ነበር ፒ 1996 ወይም ነበር ፪ 19 ዓይነት ማለት ነው

- በእርግጥ እነዚህ ድርሳናት አጣጠኙን የሐቅ መረጃ (facts) ከእርግጠኛ ምንጭ ስለሚቀዱ በደራሲው የሚኖርባቸው ተጽዕኖ ገደቡ የተወሰነ ነው።
- ተሞክሮዎቹ እንደ ቀረቡልን ሰዎች ጀግና እንድንሆን ወይም እንደነሰ ዓይነት የሕይወት ውድቀትና ድቀት እንዳይገጥመን በአስረጅነት ያገለግላሉ። (አገሌ በርግጥ ለምን ተሰናከለ ከሚል ተነስተን)
- ተሞክሮዎቹ የቀረቡልንን ሰዎች የሕይወት ጣዕም፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ ብልሃት (ጥበብ) እንድንቋደስ የታለሙ ሊሆኑም ይችላሉ። (እገሌ በርግጥ ማነው? ከሚል አጽናፍ ተነስተን)
- ተሞክሮቻች የሰዎች (ተራ) መከራ፣ ራሮት፣ ግፍና ሰቀቀን... (የጭን ቁስል... ፈተና ያልተኖረ ልጅነት የአና ማስታወሻ...)
- ገጸባሕሪያቱ ከሐሳባዊ ፖለም (ideal world) የመጡ ሳይሆን ከመካከላችን በተሞክሮአቸው መላቅ/ፈተላጊነት የተመለመሉ ናቸው!!

ልክ እንደ ግራጫ ቃጭሎቹ መዝገቡ የተመለመሉ ናቸው

ልክ እንደ የምሽት እንግዳው ነቢዮ ዓይነት (ከወጣቶች)

ልክ እንደ ሰመመኑ አቤል ዓይነት (ከፍቅረኞችና ከተጣሪዎች)

ልክ እንደ ሚክሎሲ ጉግሳ ዓይነተ (ከአብዮተኞች)

ልክ እንደ ደምበደሙ አየለ ዓይነት (ከጥቁር ደም አርበኛ)

- በእነዚህን መሰል ሥራዎች ደራሲው ከነባራዊ ዓለም ጋር ላይቃረንና ዕውነታው ላይናጋ ተጽዕኖ የማድረግ ሰፊ ሥልጣን ይኖረዋል።
- ባለጉዳዮቹ በሕይወት (በአማናዊ ሕልውና) አሉ ብለን ለመከራከር ስለማንችል፣ ደራሲው ጥበቡ ይወጣልኛል በሚለው መንገድ አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ሕሊናዊ ማንነታዝውን ይቀርጻል፣ የሕይወት መስመራቸውን ይቀይሳል፤ ዕድል ፋንታቸውንም ይወስናል። ባጭሩ የሰበአዊ ማሕደራቸውን (Profile) ሰነድ ሠርቶ ያቀርባል።
- ሁለንተናዊ መቼታቸውን (ባሕላቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ መልክአ ምድራቸውን፣ ዘመናቸውን፣ ወዘተ) ይቀርጻል።

❖ አምሳያዎችን በመመልመል ረገድ ሁለት አቅጣጫዎች ሊኖሩ ይችላሉ። አንደኛው፤ በሙሉ በሙሉ የደራሲውን የፈጠሪ ቴክኒክ መሰረት ያደርጋል። በዚህም የነባራዊው ዓለም እውነት ሳይዘነጋ።

- ፋጡራት በቀጥታ የደራሲው ናቸው
- የሴራው ጥልፍልፍ በደራሲው የሚሸረብ ነው።
- የሕይወት ውጣ-ውረዱም ሆነ የገጸባሕርያቱ መዝለቂያ በደራሲው ውሳኔ የሚጸድቅ ነው።

ሁለተኛው ለአማናውው ሕይወት የውበት ቅርጽ የመስጠት ብቃትን መነሻ ያደርጋል። በዚህ አዝማሚያ፣

- ገጸባሕሪያቱ የፈጣሪ ሕያው ፍጡራን እንጂ ደራሲው የከሰታቸው አይደሉም።
- ታሪካቸውም ቢሆን በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተሰንዶ የሚገኝ ነው
- መቼቱ በራሱ የነበረ እንጂ ደራሲው የሚመርጠው አይደለም
- የደራሲው ድርሻ
    - o የገጸባሕሪያቱን ሥነልቡና ከአማናዊው ታሪካቸው ጋር በማገናዘብ እንዲፈካ አድርጐ ማውጣት
    - o ለቋንቋው ልዩ ውበት መሰጠት
    - o ገጸባሕርያቱን እንዲቀነቁ፣ እንዲሞገሱ ወይም እነዲነቀፉ እንዲጠሉ የሚያደርጉ ጠባያት ማጉላት

<u>አጀ 1.</u> <u>አንድ ለእናቱ</u>፣ <u>የቴዎድሮስ ዕንባ</u>፣ <u>አሉላ አባ ነጋ</u>፣ ልጅነት (ዘነበ)፣

<u>አጀ 2.</u> <u>ሸርፍራፊ ወጐች</u> ታሪኮች (የጉዞ መጣጥፎች፣ የትዝብት ሂሶች፣...)

<u>የሐሳባዊ ገጸባሕሪያት አመላመል</u>

እስቲ እነዚህን አስረጅዎች እንመልከት፣

አጀ 1. እንቅልፍ ለምኔ፣ 1952፣ ገጸ 114-6፤ 142-4፤

አጅ 2. አልወለድም፣

❖ በዚህ መልክ የሚመለመሉ ገጸባሕሪያት የተሞክሮ ርዝራዥ በእኛ ተሞክሮ ውስጥ ከሞላ ጐደል ቢኖርም፤

- ጉዳያቸው ለአመክንዮ አይገዛም (ከጐረቤታችን፣ ከወገናችን፣ ወዘተ የተመለመሉ አይደሉም) ይልቅስ የደራሲውን ምኞት ለማሳካት የተሳሉ ናቸው (አልወለድም፣...)
- በጣም ይጋነናል (በእንቅልፍ ለምኔ በገጽ 142-4 የቀረበው ታሪክ ዋናውን ገጸባሕሪይውም ጻድቅ ያደርገዋል።
- የገጸባሕሪያቱ ተሞክሮ በቀጥተኛ ተዛምዶነቱ ከሚወሰድ ይቅል በተምሳሌትነት በእንቅልፍ ለምኔ 142-4 የተሳለው ሕይወት ከአሞሌ፣ ከድመትና ከላሞች ጋር ይዛመድ እንጂ በቀጥታ ስለእነሱ ለመናገር የታለመ አይደለም።
- ግልጽ የለና የታሰበበት የጭብጥ ግብ አለው።
- ገጸባሕሪያቱ የመጀጀል/የማጀጀል አጋጣሚያቸው በጣም ሰፊ ነው።

<u>አሎጐሪያዊ የገጸባሕሪያት አመላመል</u>

❖ አሌጐሪ ምንድነው

- መለያ ባሕሪየቱ ባለመነታ ፋይዳነቱ ፋቡላዊነት

  የገጸባሕሪያቱ ጥምር ሕግ ባሕርይ

  ቀላል አቀራረብ

- መማሪያዎቹ (የጠበብ ግብ ማሳኪያ)

  ሰውኛ

  ተምሳሌት

- ትረካው ፋይዳው ተፈላጊ የሚያደርገው

  ግበረገባዊ የጭብጥ ሥርይቱ

  የአጨራረስ ጣዕሙ

አሌጐሪ ልባለዳዊ ሥራችንን ለማቅረብ የምንጠቀምበት አንዱ የታሪክና ጭብጥ ማቅረቢያ ማዕቀፍ ወይም ብልሃት ነው። ብልሃቱ፣ አንድን ነገር (ሰውን፣ እንስሳን፣ ተክልን፣ ወዘተ) በሰዎች ሕይወት፣ ተሞክሮና ዓለም ተክቶ (የመሆን ያህል ወክሎ) የዚያን የወከለውን ሕይወት ነባባዊ እና/ወይም ገቢራዊ ዕውነታ በማጉላት የማሳየት የዘይቤ ሥልት ነው። ዘይቤው የመራዘሞ (extended) ባሕይርይ አለው። ከመራዘሙም የተነሳ የትረካውን ሙሉ ክልልና ገጽታ እንዲሸፍን ይደረጋል። ይህ ሁኔታ አሌጐሪዎች ሁሉ ትረካዎች መሆናቸውን ይጠቁማል፤ ኪናዊ ትረካዎች ዘይቤው ማስፈልጉ በተለይ ሥውሩን የሰው ሕፀፅ በማጉላት፣ የጐበጠውን ሰብእና በማቃናት/ለማረቅና ግብረገባዊ ጭብጥን በጥልቀት ለማስረጽና በአይረሴነት ለማለጨበጥ ነው።

በአሌጐሪ ውስጥ ታሪኩ ከተነገረለት ዓለም አልፎ ወደ ሰዎች ድብቅ የሕይወት ንጣፍ የመዝለቅ ባሕርይው በጣም የጐላ ነው። ታሪኩ የአካልና የነፍስ ያህል የተወሐዱ፣ ደግሞም የየራሳቸው የየቅል ግብ ያላቸው ሥነጽሑፋዊና ፋይዳዎች አጣምሮ ያቀርባል። በሌላ አገላለጽ መንታ የሆኑ ፋይዳዎች አሉት፤ የታሪኩ ጣዕምና የጭብጡ ድርሻ (የላዕላይና የታሕታይ ፊይዳዎች)። ላዕላይ ፋይዳው የተዝናኖት ጥማችንን ለማርካት ሲባል የሚቀናበረውን የታሪኩን ገራገር ገጽታ (ርእሰ ጉዳይ) የሚጠቁም ሲሆን ተደራሲው እንዲለቅ፣ እንዲገረም፣ እንዲሳለቅ፣ ለማድረግ ላይ ያተኩራል። ይህን ለማድረግም ምናባዊነቱ ከፍ እንዲል ያደርጋል። የታሪኩ ባለጉዳዮች ድርጊት፣ ስሜትና አቋም ኧላጅልኛ ገጽታቸውን በሚያጐላ መልኩ ይበጃጃል። ታሪኩ ሳቢና አማላየ ከመሆኑ የተነሳ ለታዳጊዎችና ለግልብ ተመልካቾች በራሱ በቂ ሊሆን ይችላል።

ታሕታይ ድርሻው ግን ራሳችንን ተመልሰን እንድንመረምርና ጉድለታችንን እንድንፈትሽ ለማድረግ ወደራሳችን የተሞክሮ ክበብ የሚመልሰን ነው። ለምሳሌ <u>በአሞራና በቅል ጋብቻ</u> ውስጠ ስለሁለቱ ፍጥረታት ታሪክ ሰምተን ስንጨርስ ተመልሰን በግልበነታችን (እንደ አሞራው) እና በሆደባሸነታችን (እንደቅሉ) ዙሪያ ያሉት ሕጻቻችን እንመረምራለን። ይህም ማለት ስለአሞራ/ቅል ታሪክ ከመስማት በመቀጠል ስለሰው የባሕርይ ጉድለቶች ፈተሻ እንጀምራለን። ይህ ታሕታይ ፋይዳው ወይም ጭብጣዊ ድርሻው መሆኑ ነው።

ኤሌጐሪ ከመንታ ፋይዳው አንፃር ሊታይ ራሳችንን የምንወርፍበት አግባ ይመስላል። ምክንያቱም ጉድለታችንን በሌሎች ላይ ለድፈን ነው መልሰን እኛው የምንሰማው። ለምሳሌ አያንቱ ዘምዘምን በአግባ ለመወረፍ ብትፈልግ፣ አጠገቧ ያለችውን ድመት በማስመሰል እንዲህ ልትል ትችላለች “ቢስ/ክፍ..... ምቀኛ! ለካፊ፤ ያንንም ያንንም መልከፍ ልማድሽ ነው!! ልክፍታም!” እነዚህ ለድመት የተሰጡት ጉድለቶች በርግጥ የድመቷ ሳይሆኑ፣ አየንቱ በዘምዘም ላየ አስተዋልኳቸው የምትላቸውን ገፀባሕሪዎች በድመት ላይ በመለደፍ ያሳየችበት የአቀራረብ ዘይቤ ነው፤ ድመት የጦስ ዶሮ (Scape goat) ናት።

አሌጐሪ ውስጠ ሰው ለመባል የማይበቁ (የሰውነት ጸጋም ሆነ አበሳ የማይመለከታቸው) ነገሮች <u>ሰውነትን</u> ይላበሳሉ፤ ይሰወኛሉ። ሰው ለመባል እንደ መስፈርት ይላበሳሉ፤ ይሰወኛሉ። ሰው ለመባል እንደ መስፈርት የምንመለከታቸው ጉዳዮች በፋይ የሚስተዋሉ ወይም በሕቡዕነት የምንረዳቸው ነቢባዊ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶቹ መገለመቻዎቸቸው ባሐሪያት ሌሎች “ገቢራት” ወይም ናቸው ገጸባሕሪያቱ የሰው አካላት ያሏቸው፣ እንደሰው የሚለብሱ፣ እንደሰው ዓይነት እንደሰው የመጠለሉ መጠለያ የላቸው ከሆኑ በፃፋ የሚስተዋሉ ናቸው። ቢመቀኙ፣ ቢያመልኩ፣ ቢያስቡ፣ ቢቀኑ፣ ወዘተ ሕቡዕ ባሐሪያት ተላብሰዋል ማለት ነው። ባሕርያት ከሕሊናዊና ሥነልቡናዊ ሁኔታዎች ጋር ይያያዛሉ። ገቢራት ደግሞ እንደ ማምረት፣ መጋባት፣ ጦርነት መክፈት፣ መደሪደር ወዘት ሊሆኑ ይችላሉ። እንደገናም ተፈጥሮአዊ ሕገባሕርያቸው ሳይፈቅድ ሲናገሩ (ሲዘብቱ፣ ሲዘልፉ፣ ሲደሰኩሩ፣ ሲደልዩ፣.....) ሲናገሩ ይስተዋላሉ።

ይሁንና ገጸባሕርያቱ መሠረታዊ ባሕርያቸውን ከሞላጐደል ማንጸባረቅ መቻል አለባቸው ታሪኩን ስንሰማ የሚጽሙት የተሰወኘ ተግባር የሚታዩን የእነሱን ተፈጥሮና ገፀባሕርይ እያሰብን ከሆነ ብቻ ነው። የምንመሰጠው። ለምሳሌ “ጅም ዐባይን ማበር” በሚለው አሌጐራያዊ ምሳሌ ውስጥ ሁለቱም የወንዝነታቸው ባሕርይ እንደተላበሱ ተሰውኝተዋል። በሌላ አባባል፣ በኤሌጐሪ ውስጥ ገጸባሐርያት ቁምር ባሐርያትን አዳቅለው ይይዛሉ ማለት ይቻላል።

ገጸባሕርያት ጥምር ባሕርያትን ሲላበሱ አንደኛው (ላዕላዮ ባሕርያቸው) የመሰውኝታቸው ነገር የትረካው ሰውኛን በመማሪያነት መጠቀም ሲጠቁም፣ በታሕታይ ባሕርየቸው ግን ከምንናርበት የሰው ዓለም ውስጥ የሚወክሉት አካል ሰው፣ ማኅበራዊ ቡድን፣ ፖለቲካ፣ አማልዕክት ወዘተ) ስላለ ተምሳሌትነት አላዝው። ስለዚህ አሌሎሪ ሰውኛንና ተምሳሌትን በአይቀሬነት መማሪያነት የጠቀማል ማለት ነው። ከሁለቱ አንዱ ጐሎ ከተገኘ ትረካው አሎሪያዊነት የለውም ብለን እንጠማለን። የሚከተለውን አስረጅ

አጅ 1. ከቤቴ በታች ከግራሮቹ (ሰውኛ አለው አሌጐሪ ግን አይደለም ፍቅር ተኝቷል ከነልጆቹ)

አጅ 2. ሳልሰመው

ሳልቅፈው

ወዳጀ ያለፈ ዘመኔ ልቤ ሰው

ልጅነት ብቻ ነው (ፈቃደ አዘዘ)

አሌጐሪን በተለይ ተወዳጅ የሚያደርጉት ሁለት ባሕሪያት አሉ። አንደኛው ሲሰወኙ የሚታይባቸው መጀጀል በጣም አዝናኝነት አለው። ጀገና ነኝ ባሉት ልክ ፈሪዎች ናቸው ብልህ ነን ባሉት ልክ ደናቁርት ናቸው ብልጥ ነን ባሉት ልክ ተጀጅለዋል። ወይም እስከዛሬ መሞኘታቸውን የሚረዱት ገና አሁን ነው (የመጥረቢያንና የዛፎቹን ታሪክ እናስብ)፤ ጠንካሮች ነን ባሉት ልክ ደካሞች ናቸው (አንበሳና ዝሆን የዘረረችውን ትንኝ እናስብ)። ሁለተኛው አጨራረሱ ነው። አሌጐራ ተደራሲውን የሚያለደምም፣ የሚያልቅ እንዲሁም አይረሴነት ያለው አጨራረስ ይኖረዋል። ብዙውን ጊዜም የመጨረሻው ገጸባሕርይ በሚናገረው ሐሳብ ወይም በሚያደርገው ድርጊያ አስገራሚነት ይቋጫል።

አሌጐራያዊ ትረካዎች ከጥንት ጀምሮ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሲስተዋሉ ይኖሩና ዛሬም በማንኛውም ማኅበራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ተፈላጊነት እንዲኖራቸው የማያደረጋቸውም በተለይ ግብረገብን ለማስረጽና ሰብአዊ ሕፀጽን ለማከም የሚያስችሉ መሆናቸው ነው።

ረጅም ልቦለድ እንደ ሥነጽሑፍነቱ ሲመረመር

- ረጅም ልቦለድ ዘለግ ያለ ትረታን (Story) ለማካተት የሚያስችል መጠነ ርዕይ ያለው የዘመናዊ ሥነጽሑፍ አንድ ዘውግ ነው እንወያይበት
- ዘውጉ ከሌሎች የሥነጽሑፍ ቤተሰብ አባላት (ከተረት፣ ከኤፒክ፣ ከአፈታሪክ፣ ከተውኔት፣ ከሕይወት ታሪክ...) ጋር የሚያዘምዱት/የሚለየት ግለወጥ ባሕሪያት ይኖሩታል።

1. ልቦለድነትንና አማናዊነት አጣምሮ የያዘ ዘውግ ነው።
    - የየቅል የማይፈቱ የሚመስሉ ነገር ግን ፈጽሞ ገጽታዎችን በአካል-እና-ሩሕነት አየቅሎ ይይዛል። እነሱም <u>ልቦለዳዊነትና አማናዊነት</u> ናቸው።
    - ልቦለዳዊነቱ ለማዝናናት ግብ ሲባል የመበጀጀት ኪናዊ ጠባዮ ሲሆን እሱም በገጸባሕርያት አመላመልና አሳሳል፣ በታሪክ አማላይነት፣ በሴራ አወቃቀር፣ በቋንቋ ትባት (ውበት) ወዘተ አማካኝነት እውን ይሆናል ልቦለዳዊነቱ

በደራሲው የቪልን ጥበብ ከማያደርጉት ነጥቦች አንዱ ከደራሲው እሳቢ በስተጀርባ ምጸታዊ ድብብቆሽ ጨዋታ ለመፈጠር መቻሉ ነው። (ቴዎድሮስ ሙላቱ)

ምሳሌ፦ልቡስ ጥለን ስናስብ የእነ በዕውቀት ብቻ የሆነው እይወት የደራሲው እሳቤ ነው።

የተጠባቢነት አቅመ ለክ የሚወሰን ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ ግን የእኛን ስምና አድራሻ ከነምግባር አያነሳም ። ግን በአሱ ገጸባህሪያት የልቦለዳዉነቱ ምስጢር በጥሬው እውነት ሆኖ አለመገኘቱ ገመናና ንድንሳለቅ ያደርግናል። የሕይወታቸውን እንስቃሴ ስንፈተሽ ግን ነው። ይህም ለማማለል ሲባል የሚደከመበት መሆኑን ጠቀሚ ነው። የከፋው ጉድ ፋጥጥ ብሎ ይታየናል። እንቆቅልሽ አለችን ደራሲ ምን አውቅልሽ አልናት እንዲህ የሚባሉ"ምን አውቅልሽ "አልናት እንዲህ የሚሉ ባሕሪያት ነበሩ ፣እንዲህ አደረጉ ዓይነት አካሄድ አለውቸቸ ፍንጨችን ተጠቅመው የመመርመር ድርሻችን እንወጣለን

- አለናዊነቱ ጭልጥ ብሎ ወደ ሐሳባዊ ዓለም የማይነጉድ መሆኑን ያጠያይቃል። ይህ ጠባዩ ቀድመውት ከነበሩት አማላይ ትረካዎች (ሮማንስ)ርቆ እንደቆም አድርጐታል ዘውጉ በሐቅና በምናባዊነት መካከለ ያለውን ክፈተት በአጅጉ ያጠበበ ከመሆኑ የተነሳ ብዙውን ጊዜ አንደ Real document historical realties ታሪዝ ሰነድ ጭምር እንዲመረምረው እንዲሁምየነባራዊ ዓለም ውኩል(Representation)እንሠደሰጠኝ ዕድል አግቷል። በዚህ ረገድ አንድ ረጅም ልቦለድ የተሳከለት ዘውግ አለ ማለት ያዳግታል።

❖ አጭር ልቦለድ ቅልብጭ ከማለቱ የተነሳ የአንድን ማኅበራዊ ቡድን የታሪክ ተሞክሮ አሳክቶ የማቅረበ አቅም አለሙ አይባልም።

❖ ኤፒክ ግርማ ሞገስና ጀብደኝነት ልዕለሰብ እና አርአያነት እያጐላ አብዝቶ የሚያደለው ወደ አማላይ ስማቶች በመሆኑ ወግ መጠረቅ ይቀናዋል። ወዳሴና የተጋነነ የማንከሰስም መሠረቱንመ የሚጥለው በአፈታሪካዊ በሚታዊና አንጡራ መገለጫዎቹ ናቸው። እናም ከኋላኛው በድንቃድንቅ ዕውነታዎች ላይ ስላልሆነ በታሪካዊ ፋይዳው የካፖታሊዝም ዘመን አኗኗር ጋር መታረቅ ቢሳነው ሊታካው ኖብል ፈለቀ የረጅም ልብወለድን ያህል ቦታ አለው አይባልም።

❖ ሮማንስ ፦ በወሲብ ፍቀር ማማለልና በፈቀር ማፈነክነክ ሐሳባዊ ጠባዩ ተውኔት የመጐራረድ የመታመቅ፣ የመቀለጣጠፍ ጠባዩ ይገታዋል።

❖ በረጅም ልቦለድ ግን ደራሱው የአማናዉውን ዓለም አመኔታ እንዳያጣ አጥብቆ የጠነቀቃል። የልቦለዱ ባለጉዳዩች ተሞክሮም ሆነ መቼታቸው ከነባር ዓለም ሁኔታዎች ጋር ተቆላላፊነትና፣ አቻዊነትና ትይዩነት እንዲኖራቸው ደራሲው አዲስና ያልነፈሰበት የአፃፃፍ ሥልት ይጠቀማል። ረጅም ልቦለድ በአፃፃፍ ሥልቱ <u>ግንብዝነት የበለትም።</u> ግኑቱም ከነባራዊው ዓለም የተገነጠለ አይደለም። ይልቅስ የዕለት ተሞክሮዎችን ያልህ የቀረበና መሠረታዊ ሐቅን በልቦለዳዊ ቅባት እያለሰለሰ የሚያቀርብ ቅርጽ ነው።

❖ ለዘውጉ ሐቅ አካልነት፣ታሪክ፣አካልነት ሰነድ አካልነት ዋናዉ ምክንያቱ ለተአማኒነት አጅጉን መገዛቱ ነው። የተአደኒነቱ መገለጫወችም የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ልዩ ማስታወሻ ፡- በ 12/06/04 የስብሐት ገ/ር ቅብርን በወ.በመኪና ውስጥ ተማሪዎች ሲያወሩ ነፈሱን በገነት ያኑረው አለት ። ሌላኛዋ እሱም ገነት እየገባም፣ እዚያ ሲደርስ ባትሪ ሎዎ ይለዋል። አአለቻት በዚህ ዕለት ከእነዚያው ተማሪወች አንዷ የካ ሚካኤል አካባቢ ስንደርስ ወደ ቤተክርስቲያኑ ዞራ አማተበችና ተሳለመች ሌላም የሚማተበው ሰይጣን ለማባረር ነው እራስሽ ሴጣን ሆነሽ የምታማትቢው ስትላት ያችኛዋ ደንቆሮ ስለሆንሽ ቅዱሳንና ሰይጣኑን ለይተሽ አታውቂመ ትላለች።

ሀ. እርግጠኝነት መገለጥ ነባራዊው ዓለም ነው መቼቱ ስለመኖሩ እርግጠኛ ነት ማመሳከሪያ ሳይንሳዊ ሰነድ አለን፡እንደ ጦቢያ ወይም እንደ ምልከአ ሰይፈ ነበልባል ወይም እንደ አልወለድም ሐሳባዊ የታሪክ የባሕልና የመልክ ምድር መቼት መሳል የረጀጅም ልቦለድ ልማድ አይደለም ። ይልቅስ እንደ ትኩሳት አንደ ይምሽት እንግዳ፣ አንደ ሚክሎል ያሉትን ልብ ይሏል የሕይወት ድርሰት የሚነበበው ባለው ዓለም አማናዊ መድረክ ላይ ተቆሞ ነው ።

ለ. የሚሳሉት ባሕሪያት አምሳወችን ወይመ አክሎቻትመንፈስ ከሚመስሉ ገጸባህሪያት ተጽዕኖ (ከጥዎቻችን) ናቸው። በገጠመኛቸው ከኛን የማየገጥመውን ከሆነ በልቦለዳዊ ፋይዳና በሐቅ መካከል ያለው ክፍተት ስለሚንበረቀቅ የጥበቡ ተአማኒነት በጥያቄ ውስጥ የገባል። ሲሳሉ ከየሐሳቦገሮችንና ከየስሜቶገሮችን በተገኙ የስብእና ተቸጽኦዎች ሆኖ ሲገኝ ግን ጉዳያቸውንና አቻ ነው። እንላለን።

ሐ. የገሕርያቱ ሰብአዊ ማንነት ፣ ተሞክሮ ሕሊናዊ ብቃትና ቋንቋ (ስብእና ፣ገቢርና ነቢብ) ተጣጥሞላቸው በሚገባ ደጀንና ግንባሩ እየተገናዘበ እንደጐላ ይደረጋል። ገጸባሕርያቱ ያላዝው ስብእና ከአፈርጁ በሚታየው (የእድሜ ክት/ት ደረጃ.....) ተሞክሮ ልክ የሚታመን ነው። ሁለንተናቸውም ከማናገሩት ቋንቋ ጋር እጅጉን የተጠቀሰው ነው። ቋንቋቸው እነሱን ያህላል፣ አነሱም የሚበያጉት በቋንቋቸው እየፈተሹ ነው። ቋንቋቸውና ሐሳበቸውም ተገነዛዛቢ ነው። የጎሩይ ወልደ ሥላሴን የጽዩንን ሞገሳና የብርሃኔ ጋብራ በቀርነቱ ላይ መነጋረራችን ከዚህ የልቦለድ መርሕ አረጋግጦ በመገኙቱ ነው።

2. ተውኔታዉነት ጐለቶ የሚታይበት ጥበብ ነው።

- ዘውጉ መጢነ ርዕየው የተዘረጋጋ /የተዘለገ ከአጽናፍ አጽናፍ የዘለቀ/ አንደመሆኑ የተለያዩ የአቀራረብ ብርሃቶችን ለስተግሃድ የሚያስችል ሆደሰፊነት አለው። የተንጣለለ/ፈርጀ ብዙ ባሕልን ፣ፍልስፍናን፣ ወዘተ .....የሚካለል / የሕይወት አዳራሽ አገር የሚያክል የተሞክሮ መድረክ ስላለውና የትኛውም ብልሃት ያልመሳቀቅ ሊያሳትፍ ይችለል። /ወግ፣ግጥም፣ታሪክ ፣ተውኔት /ለዚህም ነው ረጅም ልቦለድ ቅይጥ ዘውግ /Mixed given /ከብዙ ዘውጐች የተሚጠቀ የመሆኑ ዕድሉ መለፋቱ /Stevick , theory the novel/
- ሆኖም ዘመናዊስ ቅርጽ እንደመሆኑ፣ ደራሲው የጽዕኖ በገለፃም ረገድ ሆነ በፍልስፍና አኳያ እንዳይጫነው ብርቱ ጥንቃቄ ይሻላል። ደራሲው በዓለሙ ላይ ያለውን ተጽዕኖ አንስቶ (ከጣልቃገብነት አጀን ሰብስቦ)ለባለጐዳዮቹን ያለገደብ በሕይወት መድረካቸው ላይ እንዲተውኑ ዕድላቸውን ማስፋት አለበት። የእሱ ድርሻ መድረካዝውን ማመቻቸትና የጉዞ አቅጣጫቸውን መስመራቸውን መቀየስ ነው።

- ገጸባሕሪያት በስፋት እንዲሳተፉ ከተደረገ ደግሞ የልቦለዱ ተውኔታዉ ገጽታ ጐልቶ ይዋጣል። ታሪኩ ከዘገባነት ይልቅ ወደ ከዋኔነት ያድጋል። የባለጉዮ፣ እንቅስቃሴ፣ ድርጊት፣ ቋን ቀና ሁለንተና ሥግው የመሆን ያህል ይከሰታል። ንትርካቸው ይመጣል፣ ጥድፊያቸው ይጎዘረናል መልካቸው ይታየናል የማጣጥሙት ነገር ይጥመናል የከረሰሳቸውን ያህል የከረሰስናል የዘገነናቸውን ያህል ይዘገንነናል። ነገሮች ያ ሦስትኛ አካል ከምንጨቸው ደረሱን ማለት ነው። በሰይወት በእርግጥ አካል ነስቶ ተከሰተልን ማለት ነው። በዋናነት ደግሞ Stevick እንዳለው ሌሎች ዘውጐች ያልተሳካላቸውን ጉዳይ አሟልቷል። Novel bims a novel mainly du to its application of actions
- የዚህ መሠረቱ ደግሞ ደራሲው ጭብጥ አነፋናፊ አለመሆኑ ነው። በዘመናዊ ልቦለድ ውስጥ ደራሲው የመልዕክት ቀላጤ የግበረገብ ጠበቃ የበጐ ነገር ሰባኪ አይደለም። ድርሻው ሕይወትን እፍታዋንና ገፈቷን ገልጦ አጋልጦ በማሳየት አንባቢያንብይናዝውን እንደሰጡ ማብቃት ነው። ደራሲው አፈራራጅ እንጂ ፈራጅ አይሆንም።

3. ዝርዋዊ እንጂ ስንኛዊ አዳደለም

  - ይህም የዕውነታዉነት አንድ መገለጫ ነው። የዘውጉ የቀንቀ መጥቀት ከገጸባሕርያቱ ነባር የስብዕና መልክ ጋር የተጠቅሶ የማመነገር የወጣ እንጂ በደራሲው የየግል ቀንቋ የጋና የመግለጽ ግለ ከህሉት ላይ የሚመሠረት አይደለም። የየዕለቱ የተግባራችን አትኩረት ከተመለከቱት የሚመጣው አንዳች ተፈጥሮአዊ ውበት አለውና ደራሱ ያንን የማጐላት ዝንባሌ ያሳያል።ረጅም ልቦለድ እንዴት ይፃፍል? (ቴወድሮስ ሙላቱ)
  - ኣንድን ረጅም ልቦለድ ምልዓት ያለው ቅርጽ ሰጥቶ ለማውጣት የሚረዱ ብልሃቶች፣ <u>አላባውያን፣ መረጠና</u> ምጠና የትረካ <u>ማዕከል</u>

    1. <u>መረጣና ምጠና</u>

- ይህ ጉዳይ ተፈላጊ ቁም ነገሮችን ብቻ ከሚፈለገው ግብ አንፃር እየፈተኑ አንቀርቅቦ ማውጣትና አንድነትና ጎብራዊ አስጠብቆ የሚቀርብን ሥራ ያሳስባል። በአማናዊው ዓለም ላይ የሚታዩ ተሞክሮዎችን ሁሉ ዘርግፎ ማተት አይሞርም ። ይልቅ አቅጣጫ አመላካችና ፍንጭ ሰጪ ብልሃቶች እየተጠቀመ የተረፈውን አካል ተደራሲው በራሱ ምናብ ተጉዞ እንዲያሟላ መተው ግድ ነው። የተንዛዛ ዝርዝር ከመዘክዘክ ይልቅ ቂልፎን ምዕል አሳይቶ ከመከሰት ተስማሚ ሁኔቶችን ድርጊያዎችንና ክስተቶችን ብቻ መምረጥ ነው (የዳኛዝው ውርቁ የጽሑፍ ጥበብ መመሪያን ተመልከቱት)

    2. የትኩረት ማዕከሉን በጥንቀቄ ማስተዋል።

- ረጅም ልቦለድ <u>የሰበት ማዕከል</u> (center of gravity) አለው። ማዕከሉ አንድ ወይመ ሁለት ውሱን ገጸባሕሪያት ይሆናሉ። አንዱ ወይም ውሱኑ ገጸባሕርያት የታሪኩንና የራሴው አቅጣጫ የሚመራ አውሪ ሚና ያላቸው ናቸው። (በገረ ውስጥ ተመስገን ልብ ይሏል)። በልቡስ ጥላ ደግሞ በዕውቀትን ሚልኪንና መልካምን ይጠቅሳል።አንድን ልባለድ አማክሎ የሚመራ ጭብጥ ይኖራል ጥብጡ ተጠሪ አለው የማዕከሉ ባለቤት የሆነ ገጸባሕርዩ

- ስለሆነም አንድ ልባለድ ሲፃፍ ታሪኩን አስተባብሮ ሊመራ የሚችል ጠንከራ ደራና ግብ ያለው የትኩረት ማዕከል መመረጥ አለበት።

3. አግባብነት ያለው አንባር

- ይህ የታሪኩን ባለጉዳይ የታሪኩን ተጠየቅ፣የመዋቅሩን አደረጀጀት የገጸባሕርያቱን የስማትና ዝንባሌ አቅጣጫወች ማየት እንድትችል አኩረታችንን አቅጣጫዎች ማየት እንድንችለ ትኩረታችንን አቅጣጫ የሚሰጥልን አካል ነው።

4. ገለፃ /exposition /
5. ጡዘት
6. ግጭት

<u>አጭር ልቦለድ</u>

አጭር ልቦለድ በተመለከተ ለናገር ዙሪያ መላስ ጐደዩችን መደስ ያሻል። አነሱም ሥነጽሑፍን ከነትረካነቱ ግለወጥነቱን የተመለከቱት ነጥቦች ናቸው።

1. አጭር ልቦለድ እንደ ሥነጽሑፍ ጥበብነቱ ሲመዘን

- የተገዘኖት ሥራ የጥበብ ውጤት የቋንቋ ውበት የሚያመነጨው የድርሰት ሥራ ነው።
- የደራሲው የምናብ ዓለም ትዕይንቶች በወረቀት ላይ ሲከሰቱ ሊተወሪ የሲወኑ የሚታይበት የፈጠራ ሥራ ነው።
- በደረቁ ሲታይ ውሸት መስሎ በተዘዋዋሪ አንድምታው ግን እውነት ሆኖ የሚነበብበት ድርሰት ነው።
- የደራሲውን የመንገር የማስተማር ወይም መረጃ የማቹጐድጐድ /ቅርጽ አዲስ ዓለም ገጽታ መልሰን እንድንፈጥር ማገዝ ነው።/ተግባር ማለዕክት ማወጅ ሳይሆን ወሳኝ ፍንጨችን ፈንጥቆ ራሳችንን ተግባራት ላይሆን ይለቅሳ ለሐይወት አዲስ ጣዕም ብርቅዬ ገጽታ ሰጥቶ ጭብጥን በጥበብ አላዝቦ የማቅረብ የፈጠራ ተስጥኦና የአቀራረብ ክልሎትን ግድ ይላላ።
- የማፍታቻ ጥያቄ መከለሻ.....

2. አጭር ልባለድ እንደ ከኪነትረካነቱ ሲብራራ

❖ አጭር ልቦለድ ኪናዊ ትረካ ነው።

ትረካ ከጣዕም አንፃር በሁለት ይከፈላል

ቴክኒካዊ ትረካ
- የዕውቀት የመረጃ፣ የክሂሎች ማስጨበጫ ጣዕም ግለጽ፣ ቀጥተኛ፣ እማሬያዊ ጣዕም ያለው ትረካ

ኪናዊ ትረካ
- የተገዘናኖት ጣዕም የሚያመነጭ ተዘዋዋሪ፣ ፍካሬያዊ ጣዕም ያለው

- ኪናዊ ትረካ
    - የደራሱው የምናብ ውጤት ነው።
    - ከነባራዊ ዓለም ጋር ትዩዩነት ያለው እንጂ ቅጂ አይደለም
    - በፍንገጣ የተሞላ ነው፣ያልነበረው ሆኖ የነበረው ተሸሮ ይቀርብበታል
    - ተደራሲን ተቀባይ ሳይሆን የምናብ ተሳታፊ ይደርጋል
    - ዓለምንና ሕይዋትን ካልታዩበት ማዕዘን ለማሳየት አዘውትሮ በመትጋት አዲስና ያልለዘዘ፣ የልነፈሰበት ገጠመኝ ያቀርብልናል።
    - የትረካ አለባውያንን በምልባት ያሳትፋል፤ እነሱም ገጸባሕርይ፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ አንባር፣ መቼት፣ ግጭት ሴራ፣ ጭብጥ የመሳሰሉት ናቸው።
- በአነዚህ ባሕርየቱ እንደ ረ/ልቦለድ እንደ ተረት፣ እንደ ሚት፣ እንደ ትርክት (anecdote) እንደ አፈታሪክ፣ ወዘተ ሁሉ በኪተትረካነት (narrative) ይመደባለ፤ በአዝናኝ ትረካነቱ ይታወቃል።
- ጥያቄ፣ ማፍታቻ፣ መከለሻ...

3) አጭር ልቦለድ እንደ ግለወጥ ዘወግነቱ (Short story as an independent/unique genre)

- እርግጥ አጭር ልቦለድ ሥነግጥማዊ ጥበብን ይመስላል፤ እንዴት?
    - ምጥን ቅርጽ ኖሮት ግን በይዘቱ ጥልቅ ነው፤ ከአካሉ ቁጥብ፣ በነፍሱ ግን ጥልቅ ትርጉም የሚላበስ በመሆኑ፤
- እርግጥ አጭር ልቦለድ ተረትን፣ ፋቡላን፣ ትርክትንና ቀልድን ይመስላል፤ እንዴት?
    - ጠባብ መጠነ ገጽታ ያለው ተሞክሮን ብቻ ያካለለ ስፋት አለው
    - ነጠላ ወይመ ልል ሴራ ይሸረብበታል
    - አንድ ጥያቄ ብቻ ይነሳበታል፤ ያጥያቄ ሲመለስ ትረካው ያበቃል።
    - በጥቂት ገጸችና በተወሰኑ ቃላት ተቀናብሮ ይቀርባል።
- እርግጥ አጭር ልቦለድ ረጅም ልቦለድ የሚጐራበቱ ባሕሪያት አሉተ፤ ምን-ምን?
    - ተአማኒነት የላዠው ተሞክሮዎችን ያነሳል (ያቀርባል)
    - የሰዎች መጀጀልም ሆነ ብልህነት ከነባራዊው ዓለም ጋር ትይዩና አቻነት ያለው ነው።
    - ምክንያታዊ የሆነ የግጭት-የክረት-የመፍትሔ ሂደት ይስተናገድበታል፤ የሕይወት ውጣ-ውረድ <u>አመክንዮአዊ</u> ነው።
    - ጠቅላላ ገጽታው በዕውነታ ላይ የተመሠረተ ነው፤ መሰመር የተሳተ አማላይነት፣ የተጋነነ ጀብደኝነት ወይም አይታመኔ ዓለም አይዘወተርበትም።
- ሲጠቃለል፣
    - በእርግጥም በብዚ ባሕርያቱ አጭር ልቦለድ ከሌሎቹ የሥነጽሑፍ ጥበባት ጋር የሚያመሳስሉት፣ የሚጐራብቱት ወይም ቤተኛ የሚያደርጉት ጉዳዮች አሉት።

- ያም ሆኖ ታዲያ፣ አጭር ልቦለድ ይህን ዘውግነቱን (ዘርፍነቱን) ይዞ እንዲገኝ፣ በዚህ ስሙ ተለይቶ እንዲጠራ የሚያደርጉት ባሕሪያት አሉት። ምንድናቸው?

1. ዘመናዊ ዘውግ ነው፤ ሲባልስ?
   - እነ Holmes እንደሚያነሱት በአንዳንድ ባሐርያቱ ተስተወራዋል ቢባልም፤ እንዲሁም መሠረታዊ ባሕርየቱን የቀዳው ከተረት ነባር/አንጡራ ገጽታዎች ነው። ቢባልም፣ ይህ ዘውግ ተጀመረ የሚባለው በአሜሪካዊው አለን ፖው (1809-1849) ዘመን ነው፤ 19 ኛው ክ/ዘመን ማለት ይሆናል።
   - መነሻውም የዘመናዊውን ሰው ተሞክሮ ለዕውነታ በቀረበ አኳኋን ቀርጾና ገልጦ በማሳየት ላይ ያተኮረ ነበር። ዛሬም በዚያ ፍልስፍና ዙሪያ የሚያጠነጥነው ባሕርይው እንደጠና (እንደ ጐለበተ) ይገኛል።
   - ዘመናዊ ነው የሚያሰኘው ሌላው ነጥብ በዝርው ትረካ መቅረቡ ነው፤ አጭር ልቦለድ በስንኝ የመዋቀር ልማድ የለውም።
   - በታችኛው መደብ ዘወትራዊ ውሎና ተሞክሮ ላይ ማተኮሩም አንዱ የዘመናዊነቱ መገለጫ ነው።

❖ በዚህ የተነሳ አጭር ልቦለድ ተረት ወይም ሚት ወይም አፈታሪክ አይደለም።

2. ጠባብ መጠነ ርዕይ ይሸፍናል፤ በም ይረጋገጣል?
   - ከመቼት መቼት የሚዘዋወር ይዘት የለውም
   - በአንድ ግጭትና በነጠላ ሴራ ብቻ ይዋቀራል
   - አንድ የተሞክሮ ዘለላ (ዘርፍ) በቻ ይመዛል
   - ገደቡ (የትረካው) በግልጽ የተከለለና የተመለከተ ነው።
   - አንድ ጥያቄ ያነሳል፤ በነጠላ ውጤት (መልስ) ይቋጫል?

❖ በዚህ የተነሳ አጭር ልቦለድ አፈታሪክ ወየም ረጅም ልቦለድ ወይም ሚት ከመሆን የወጣ ነው።

3. አጭር ልቦለድ አጭር ብቻ ላይሆን ጥድፊያ ያስተዋልበታል፤ ምን ለማለት?
   - ቁጥብነት ዋናው ባሐርይው ነው፤ ሲዘረዝረ፣ ሲገልፅ፣ ሲያብራራ አይገኝም
   - በአንድ ቅምጥ አንብበን የምንጨርሰው ነው።
   - ገለፃው፣ ምልሱ፣ ሐተታው ምጥን ሆኖ ግን በድርጊት የበለጸገ፣ በተጨባጭ ክንዋኔዎቹ የታገዘ ይሆንና ተውኔታዊ ገጽታው እንዲጐላ ይደረጋል።

ማበልጸጊያ አስረጅ

የሚከተሉት ንድፎች እንመልከትና የትኛው ለአጭር ልቦለድነት ቢታጭ ትክክል ነው ብለን እናንሳ።

<u>አጅ 1</u>፡- አበበ በሶ ይወዳል።

ለበሶ ሲል ገብስ ማምረቱ ብዙ ውጣህውረድ አስከተለበት።

ውጣ-ውረዱ ስለመረረው በሶ እርግፍ አድርጐ ተወ።

አጅ 2፡- አበበ በሶ ውል አለው።

በሶ ፍለጋ ወጣ።

በሶ ለብሶ ሰው እየተሳለቀበት ተመለሰ።

❖ ጥያቄ፣ ማፍታቻ፣ መከለሻ.....

የአጭር ልቦለድ አለባውያንና የተለየ ባሕርያቸው

❖ አጭር ልቦለድ አለባውያንን በማሳተፍ ረገድ ከሌሎቹ የትረካ ዘርፎች የተለየ አይደለም፤ የሚለየው "ምን ዓይነት አባውያን በምን ዓይነት ብልሃት ያሰማራል?" በሚለው ነጥብ ነው።

❖ ዐባይት አለባውያኑን እየጠቀሰን ባሕርያዝውን እንፈትሽ

1. ገጸባሕርይ፡- በታሪኩ ውስጥ ዋናው ባጉዳይ፣ ባለታሪክና ባለሚና አካል ገጸባሕሪይ ይባላል።

❖ ገጸባሕርያት ለአጭር ልቦለድ ሲመለመሉ ምን ምን ጉዳዮች መታወስ አለባቸው?

ሀ. ሚናቸውን መወሰን ያስፈልጋል፤ ዐብይ ባለጉዳይ ናቸው ወይስ ንዑሳን ባለድርሻዎች?

ለ. ከነጠላው ተሞክሮ፣ ከነጠላው ግጭትና ከነጠላው ውጤት አኳያ ብቻ ተመልክቶ ሚናቸውንና ጽል/ሽንፈታቸውን በግልጽ መወሰን ያሻል።

- የገጸባሕርይው ጠቅላላ ሰብአና ሲታይ ጀግና ሊሆን ይችላል፤ ግን በአጭር ተሞክሮ ውስጥ ሊፈራ፣ ሊያፈገፍግ፣ ሊሸነፍ ይችላል።
- ገጸባሕሪይው ጭምት፣ ጨዋና ክብሩን ጠባቂ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም በአንድ አጋጣሚ ተጀጅሎ ሊዋረድ፣ ሊሳቅበት፣ ወዘተ ይችላል።
- የገጸባሕርይው መልክ፣ ቁመና፣ ጽሞና፣ ጅልነት ወዘተ የሚያስፈልገው ለዚያች የልቦለዱ የተሞክሮ ዘለላ ከተፈለገ ብቻ ነው። (አጭር ልቦለድ ቁጥብና ለጋሽ እንደመሆኑ የተንዛዛ ገለፃ አያስፈልገውም)፣ የመታወቂያ ፎቶ ግራፍ ሙሉ ቁመና እንደማያሻው)
- የሚያስፈልገው አካላዊ፣ ባሕርያዊና ሥነልቡናዊ ቅጥንብራቸው ግን ግልጽ ብሎ መከሰት አለበት፤ በድርጊቶችና በታሪኩ ላይ ያለው ተጽዕኖ እንደዱታይ

ሐ. ወሳኝና ውለኛ አካላት ብቻ ወደታሪኩ ይቀላቀላሉ

- ወለም-ዘለም፣ ብልጭ-ድርግም፣ ሂድ-መጣ የማሉ ገጸባሕርያት ይከላሉ፤ መቼትና ክልል ስለሌለ
- ውለኛዎቹ ባጉዳዮች ጉዳያቸውን ሲፈጽሙ፣ ታሪኩ ያበቃል/ያከትማል።

መ. ደራሲው ገጸባሕርያቱን ከዚያች የተሞክሮ ዘለላ አንባር ያላቸውን አቋም፣ ስሜት ውሳኔና አዝማሚያ ጠንቅቆ ማወቅና በቅርበት መረዳት አለበት።

ሠ. ለገጸባሕርያቱ ሰፊ ዕድል መስጠት ከደራሲው ይጠበቃል።

- በቋንቋና በድርጊት ሲሳተፉ መታየት አለባቸው
- ፍልስፍናው የደራሲው ሳይሆን የእነሱ ሊሆን ይገባል።

2. ታሪክ፡- የገጸባሕሪያቱ <u>የጉዳይ፣ የተሞክሮና የድርጊት ሂደት</u> የሚቀርብበት ሐተታ ነው። ማንንም ተደራሲ የሚማርከውና እንዲከታተልም የሚገፋፋው ይኸው የሂደት አቅርቦት ነው።

❖ የአጭር ልቦለድ ታሪክ በድርጊት የታጀበ (የተሞላ)፣ ፍታሽነት ያለው (በፍጥነት የሚገሰግስ)፣ ግራ-ቀኝ የማይጠማዘዝ (ጐኖዊ ጉዳዮችን ማየነሳ)፣ አንድን ነጠላ ጥያቄ ለመመለስ ወደፊት የሚንደረደር ሊሆን ይገባዋል።

3. ቋንቋ፡- የታሪኩን ፍሰት የምናቀርብበት፣ የምናሻግርበት፣ የተግባቦቱ መማሪያ መሆኑ ነው። ትረካው በሥዕል ወይም በሌላ ምልክት አይተረክም፤ በቋንቋ ብቻ ነው።

❖ ቋንቋው ቁጥብ ነው።

- ቃላቱ፣ ሐረጋቱ፣ አንቀጾቹ ሊጐረዱ ቢችሉ አያሰወቅስም፤ የዘወጉ ባሐርይ ነውና። ሆኖም ወሳኝ ስሜትና አቅጣጫ ጠቋሚ የሆኑት ገለጻዎች መካተታቸው አይዘነጋም።
- ከ"ፍዝ" ቃላት ይልቅ የድርጊት ቃላት በጣም ይመረጣሉ።
- የገጸባሕርያቱ ቋንቋ ጐልቶ መታየትና ሰፊ ድርሻ ማግኘት ይኖርበታል፤ በተለይ ምልልስ ዋጋው ከፍ ያለ ነው። የእነሱ ቋንቋ የወለዳቸውን ባሕል ያሳደጋቸውን እሴት በማሳየት ረገድ ወደር ሊኖረው አይችልም።
- የደራሲው ቋንቋም ምጥን ያለ፣ በሥዕላዊነት የበለጸገና ምናብ ከሳች እንዲሆን ይጠበቃል።

4. መቼት፡- ውሱንና ሰፊ ጊዜን፣ ጠባብና የተዘረጋጋ ቦታን፤ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ታሪካዊ ዳራዎችን ሁሉ የሚያቅፍ ጽንሰሐሳብ ነው። ገጸባሕርያቱን በአካልም ሆነ በመንፈስ፣ በሥጋም ሆነ በነፍስ ወስኖ የሚያስቀምጣቸው ሁለንተናዊ ክልል ነው። መቼት በብቃታቸው፣ በሕልውናቸው እንዲሁም በተግባራቸው ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ አለው።

❖ በአጭር ልቦለድ የመቼት ክልል ለተወሰነው የተሞክሮ ዘለላ ብቻ የሚመጥን ነው፣ አይቀርፆቹን የመቼት ክልልሎች ብቻ ያቅፋል።

❖ መቼቱ ገጸባሕርያቱን በተጨባጭ የሚከሰትና ተግባሮቻቸውን በጉልህ የሚያመሰጥር ሊሆን ይገባጭ።

❖ መቼቱ በተሞክሮው ላይ ያለው የድባብሞ ሆነ የተጽዕኖ አንድምታ ታስቦበት ሊሠራ ይገባል።

- በ"አበበች ታሪክ" የምድር- የሰማይ ድባብ መን ተጽዕኖ

5. አንባር፡- <u>ማን ከየት አንባር</u> ሆኖ ታሪኩን ነገርን ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጠን ነው። በማንኛውም ልቦለድ አንድ <u>ወሬ ነጋሪ አለ</u>። (ሁለት ተግባራት አሉት)

ግልጽ ተግባር (ታሪኩን አምጥቶ ይነግረናል)

ሥውር ተግባር (አዝማሚየውን ያንጸባርቃል)

* ገጸባሕርያቱን እንድንጠላ/እንድንወድ ተጽዕኖ ያሳድራል።

አስረጅ **1**፡- ፈራቻቸው። ፊታቸውን በሙሉ ተላጭተውት የሚያስቀሩት..... ጥቁር ንፍጥ የምትመስል... የፀጉር ሥዕል ብቻ ናት (ማኅሌት 41)

አስረጅ **2**፡- ውሽቷ በዳዴ የሚሄድ ሳይሆን፣ ነፈስ ዘርቶ ቆሞ የሚሄድ ነው (የማለዳ ስንቅ ገጽ 91)

- የአጭር ልቦለድ ወሪ ነጋሪ፣

  ሀ. ገጸባሕርያቱን *መ*ጋፋት (ዕድላቸውን *መ*ሻማት) የለበትም፣ ለእነሱ ተራፍጆታ የበለጠ ቦታ ሊሰጥ ይገባል፤ ትረካውን ተውኔታዊ ለማድረግና ገጸባሐርያቱን በጉዳያቸው ዙሪያ እንዲጋፈጡ ለማረግ ሲባል።

  ለ. የአድልኦ "አንባሩን" *መ*ቀነስ አለበት፤ ከስሜት ነፃ ሆኖ ሚዛናዊ አቋም ሊኖረው ይገባል።

  ሐ. የአዋቂ ኩሉ ግንባር ይልቅ ከፋል አዋቂ ኩሉ ግንባር ይመረጣል፤ እንደ አምላክ ሁሉን ገጸባሕርያቱ ያውቃሉ፤ በከፊል ተደራሲያኑ ይወቁ የሚለውን አማራጭ (አዝማሚያ) ሊከተል ይገባል።

6. ግጭት፡- በሕይወት አስገዳጅነት የተነሳ በአካላት (በሰውና በሰው፣ በሰውና በተፈጥሮ፣ በስውና በራሱ ወዘተ) *መ*ካከል የሚፈጠር የእሰጥ-አገባ ወይም የግብግብ ሂደት ነው። ግብግቡ ሲጠነክር ወደ ፍልሚያ፣ ፍልሚያው ሲበረታ (ሲጧጧፍ) ወደ ሴራ ይረማመዳል። በልቦለድ የሚፈለገው ግጭት እንዲህ ዓይነት ተራዛሚ ውጤት ያለው ነው።

- ለአጭር ልቦለድ የጠፈ ግጭት አብነቱ ነው (ዐብይ የተወዳጅነቱ ምንጭ)።
- የአጭር ልቦለድ ግጭት ነጠላ ነው። እንዴት ምላሽ ብቻ ይጠበቅበታል።
- ግጭቱ ወዲያው ተግ ብሎ በፍጥነት *መ*ቀጣጠል አለበት፤ የኔ ተደራሲውን የሚቅበጥበጥ (ፋታ የመንሳት) ጉልበቱ ይጨምራል።
- ከፍጻሜ አስከሚደርስም በፈጥነት ከአንዱ ርከን ወደሌላዙ ሳያስልስ *መ*ሸጋገር ይጠበቅበታል፤ *መ*ጠማዘዝ ወይም ጐናዊ እንጃ-ግራንጃ ማንሳት የለበትም።

7. ሴራ፡- ግጭት እየበረታ፣ እየከረረ ሲሸጋገር የሚፈጠር የፍቅር የጠብ *መ*ሠረት ያለው የግብግብ ጥልፍልፍ ነው።

- በአጭር ልቦለድ ውስጥ ድርብ-ድርብርብ ባሕርይ የለውም።
  - የሚፈጠረው ግጭት ነጠላ ስለሆነ ሴራውም ነጠላ ነው።
  - የሚያልላቸው የውስበት፣ የጡዘትና የቅልበሳ ደረጃዎች በፍጥነት ይሸጋገራል።

አጫጭር ልቦለዶችን

- ለይቶ ማውጣት
- *መ*ገምገም/*መመ*ዘን
- በራስ ተነሳሽነት ለ*መ*ጻፍ *መ*ሞከር